# ታጠቅ - ኢትዮጵያ

## ታጠቅ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር ልሳን

ታኢ ቁ.2

## ራዕያችን ዴሞክራሲያዊ አንድነታችን

ህዳር 1999

ታጠቅ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር ለኢትዮጵያዉያን ዘላቂ ሰላም፣ ነጻነት፣እኩልነትና ደህንነት የቆመ ድርጅት ነዉ:: ራዕያችንም:-

ዲሞክራሲና ፍትህ የሰፈነባት የዜጎች ሁለንተናዊ መብቶች የተከበሩባት እንደ ሰንደቅ ዓላማ መለያችን እየሆነ የመጣው ጦርነት ረሀብ በሽታ ኋላቀርነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተወግደው ልጆቿ  በሰላምና በኩራት የሚኖሩባት ሰዎች በዘረ-ማንነታቸው ሳይሆን በሥራቸውና በዕወቀታቸው ደረጃ (የሚመዘኑበት) ብሔረሰቦቿ በመፈቃቀርና በመተሳሰብ በአንድነት በጋራ የሚኖሩባት ኢትዮጵያ ተገንብታ ማየት ነዉ::(የታኢዴአግ ፕሮግራም)

ይህንንም ለመተግበር ታጠቅ ዝርዝር የፖለቲካ ፕሮግራም አዉጥቶ ዓላማዉንና የመታገያ ዘዴዎቹን ተልሞ በመታገል ላይ ይገኛል:: እነደ ታጠቅ አመለካከት የፖለቲካ ዉጤት የሚጀምረዉ በጠራ አመለካከት ነዉ:: ዓላማን ከመጀመሪያዉ ግልጽ አድርጎ ማስቀመጥን ይጠይቃል:: በፕሮግራማችን እንደተገለጸዉም ዓላማችን ራዕያችንን በተግባር ለመተርጎም ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል:-

- በኢትዮጵያ ዲሞክራሲና ፍትሕን ማረጋገጥ
- የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች በእኩልነትና በአንድነት እንዲኖሩ ማድረግ
- የኢትዮጵያዉያንን ሰብአዊ መብቶች፣የፖለቲካ፣የኢኮኖሚና ሶሻል መብቶች ማረጋገጥ
- ረሃብን ማስወገድ
- በሽታና ኋላ ቀርነትን መቀነስ
- በዘር፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወዘተ. የተመሰረተ አድልዎን መዋጋት
- ሙስናን መዋጋት
- በማሕበረሰቦችም ሆነ በአገራት መሀል የሚኖሩ ግጭቶች የሚፈቱበትን ሰላማዊና ዲፕሎማሲያዊ መንገድ መሻት፣ ሌሎች መንገዶች በበቂ ምክንያት ላይ የተመሰረቱ የመጨረሻ የመከላከያ እርምጃዎች መሆናቸዉን ማረጋገጥ

Tatek Ethiopia Information Centre,
PO Box 4281, London WC1N 3XX    e-mail: Tatekethiopia@hotmail.com

ይህንን ዓላማ በተግባር ለማዋልም ጥርት ያለ እስትራተጂና የትግል ስልት ማዉጣትን ይጠይቃል። በኛ አመለካከት፣ ከዚህ በፊት በብዙ ክፍሎች የቀረበና ትግል የተደረገበት፣ የሰላምና እርቅ ጉባዔ መጠራት አገራችን ላለችበት ሁኔታ ትክክለኛ እስትራተጂያዊ ግብ ነዉ እንላለን። ሆኖም ግን ይህ እስትራተጂያዊ ግብ የተነሳንበትን ዓላማ ወይም ራዕያችንን እዉን እንዲያደርግ ወይም ከራዕያችን ጋር እጅና ጉዋንት እንዲሆን ከተፈለገ የጉባዔዉን ዓላማ ማብራራት የግድ ነዉ። በኛ በኩል የጉባዔዉ ዓላማ በሕብረሰባችን መሐል ያሉ የተለያዩ ቅሬታዎች በሰላማዊ መንገድ በመፍታት የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደ እኩልነትና ዴሞክራሲያዊ አንድነት ለማሸጋገር፣ለዴሞክራሲያዊ ሕገመንግስታዊ ሥርዓት የሚያበቃ ጉባኤ ነዉ እንላለን። ስለዚህም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት የተብራራዉ የእስትራተጂ አካል እንደመሆኑ መጠን የጉባኤዉ መጠርያ መሰረት ነዉ። በዚህም መሰረት ላይ ተመርኩዘን የኢትዮጵያን ሕዝቦች አንድነት እናጠናክራለን። በዚህም የተብራራ ግብ ዙሪያ እስትራተጂክ ግብረ አበሮቻችንን (ፓርትነርስ) ያቀፈ የጋራ የትግል ትብብር ወይም ሕብረት ዉስጥ እንሳተፋለን።

በእስትራተጂ ደረጃ መተባበር የሚያስችል የጋራ ዓላማ ከሌለን ክፍሎች ጋር ደግሞ፣ በተቻለ መጠን ወገንን ማስፋት ተቀዋሚን ማጥበብ በሚለዉ መርህአችን መሠረት በስልት ደረጃ ተመሳሳይ ሃሳብ ከምንጋራዉ ኃይሎች ጋር ትብብር በማድረግ የስልት አበሮችን እንመሰርታለን። ሆኖም ግን ስልት ለእስትራተጂ ተገዥ በመሆኑ በስልት ደረጃ የምንወስደዉ እርምጃ ወይም የምናቀርበዉ ሃሳብ ለእስትራተጂያዊ ዓላማችን እንቅፋት እስካልሆነ ድረስ መሆኑን ማስመር እንፈልጋለን።

በነዚህ መሠረተ አስተሳሰቦችና መመሪያዎች ላይ በመመርኮዝ ታጠቅ የኢሕአዴግን አምባገነንነት ከሚታገሉ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ጋር ለመቀራረብና አብሮ ለመሥራት፣ በፕሮግራምና ስልትም ከሚመሳሰለዉ ጋር ደግሞ ለመዋሃድም ዝግጁ ነዉ። ታጠቅ እራሱ የድርጅቶች ዉህደት ዉጤት ነዉ። ታጠቅ ባንድ ድርጅት ወይም ጥቂት ድርጅቶች ወደ ስልጣን መቆናጠጥ ዘላቂ ሰላምና ደህንነት በኢትዮጵያ ይሰፍናል ብሎ አያምንም። ህብረሰባችን የሚፈልገዉን መረጋጋትና እድገት ለማግኘት መፍትሔዉ በመሰረታዊ የዲሞክራሲ፣የሃገር አንድነት፣የመድበለ ፓርቲ ወዘተ.ጥያቄዎች የኮንሴንሰስ ፖለቲካ ነዉ ብሎ ያምናል። በዓለም አቀፍ ደረጃም ታጠቅ እስትራተጂክ ዓላማዉንም የሚቀበሉ መንግስታትም ሆኑ ድርጅቶች ጋር አብሮ ለመስራት ዝግጁ ነዉ።

ታጠቅ በሁለገብ ትግል ተሰማርቷል። በሕጋዊና በሕገ ወጥ መንገድ ኢሕአዴግን ማዋከብና የኢትዮጵያን ሕዝብ ለእዉነተኛ ሥልጣን ማብቃት ይገባል ይላል። ለዚህም የጦር ኃይሉን በመገንባትና በማዋጋት ላይ ይገኛል። የሕወሐት/ኢሕአዴግ የጦር አባላት መሳሪያቸዉን ወደ ጨቋኙ ኢሕአዴግ እንዲያዞሩና ከጎኑ እንዲቆሙ ጥሪዉን ያቀርባል።

የግንቦት 1997 የሕዝብ ድምጽ የመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለማያወላዉል አንድነት የሰጠዉ ድምጽ ነዉ። የግንቦቱ የሕዝብ ድምጽ ለዴሞክራሲና እኩልነት የሰጠዉ ድምጽ ነዉ። የግንቦቱ የሕዝብ ድምጽ ለኢትዮጵያ ሰላምና ብልጽግና የሰጠዉ ድምጽ ነዉ። ኢሕአዴግ በሕዝቡ ድምጽ የሚሸነፍ መሆኑን ሲረዳ ሕዝቡ በትግሉ የተጎናጸፋቸዉን የዲሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች በአመጽ ቀምቷል። ሕዝቡንም ከነመሪዎቹ ጨፍጭፏል፣አስሯል፣አዋክቧል።ታጠቅ የሕዝቡን መብት ለማስመለስ፣ ለብሶቱም ምላሽ ለመስጠት ታጥቆ ተነስቷል።

ይህን የወቅቱን የሕዝብ ጥሪ በመቀበልና በእስትራተጂያዊ ዓላማ ዉስጥ በማካተት፣ መሰረተ መርህዎቹን የተከተለ የተግባር ክንዉኖችን አዉጥቶ ታጠቅ ለሕዝብ መብት በመታገል ላይ ይገኛል። በማያባራ አመጽ ላይ የቆመ የመብት ረገጣን ለመከላከል የሚደረግ የትጥቅ ትግልና በሰላማዊ መንገድ የሚደረግ ትግል ለሰላም እስከተነጣጠሩ ድረስ፣ የማይነጣጠሉ የትግል ዘዴዎች ናቸዉ ብሎ ታጠቅ ያምናል። ሁለቱም የትግል

ዘዴዎች አመጻኛዉን መንግሥት ጣብቂያ ዉስጥ በማስገባት ከድርድር ዉጭ ሌላ አማራጭ እንደ ሌለ እንዲገነዘብና በሰላማዊ መንገድ ለሕዝብ ሥልጣኑ የሚሸጋገርበትን መንገድ እንዲፈልግ ያደርጋሉ ብሎ ታጠቅ ያምናል። አልያም አሻፈረኝ ካለ፣ እጣዉ መደምሰስና የሕዝብ ሥልጣን መከበር ይሆናል።

ይህንንም ገድል ለመወጣት የተቃዋሚዉ ግንባር መጠናከር ወሳኝ ነዉ። በድርጅቶች መሐል የሚፈጠሩ ልዩነቶች የጋራ መድረክ አግኝተዉ እንዲስተናገዱ በማድረግ ወደ ዋናዉ ፍልሚያ እንዲተኮር ማድረግ አስፈላጊ ነዉ። ከዚህም አኳያ ዛሬ ሕዝባችን ተስፋ የተጣለባቸዉ ድርጅቶች መሐል የሚካሄደዉን መነካታተል እንዲሁም  በቅንጅት አባላት መሐል ያለዉን መልሶ አብሮ የማያሰራ አይነት ፍልሚያ ታጠቅ ያወግዛል። ሁላችንም ይህን አይነት ከንቱና ትግላችንን የሚጎዳ የእርስ በርስ ፍልሚያ አጥብቀን ልናወግዘዉ ይገባል። ሰዉ ከተደራጀ  ልዩነቶች አይኑሩ አይባልም። ነገር ግን ሁሉም ነገር ካለዉ ይዞታ (ከኮንቴክስት) ዉጭ ሊሆን አይችልምና አሁን በዚህ ሁኔታ መለያየቱ አብሮ መስራት ስለማያስችል፣ አብሮ ሊያሰራና ወደ ኢሕአዴግ ማትኮር በሚያስችል ሁኔታ ልዩነቶቹን ልናስተናግድ ይገባል። ያለበለዚያ ተጋጭዎቹ የኢሕአዴግን ሥራ ማቅለል ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝብ ተስፋ በማስቀረጥና ለከፋ አደጋ ይጥሉታል። ታጠቅ አብሮ መስራትንና አንድነትን ለማጠናከር መወሰድ ባለባቸዉ እርምጃዎች ላይ ሁሉ በኃላፊነት ስሜትና በቀናነት የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ቃል ይገባል።

የታሰሩት የሕሊና/የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

Tatek Ethiopia Information Centre,
PO Box 4281, London WC1N 3XX e-mail: Tatekethiopia@hotmail.com